# የህዳሴው ግድብ የቆየውን “ጨዋታ” ቀይሮታል

**ሰላም አበበ 1/1/14**

ኢትዮጵያ አባይ ወንዝ ላይ እየተገነባች የሚገኘውን የህዳሴው ኃይል ማመንጫ ግድብን በተመለከተ በግብጻዊያን ዘንድ የተለያዩ አመለካከቶች ይንጸባረቃሉ፡፡ በርካታ የግብጽ ህብረተሰብ ክፍሎች የግድቡ ግንባታ ሀገራቸው ላይ ጉዳት እስካላስከተለ ድረስ ኢትዮጵያ ግድቡን ብትገነባ ችግር አይኖረውም የሚል እምነት እንዳላቸው መግለጽ ጀምረዋል፡፡

ሌሎች በእኔ ምልከታ ጥቂት ሊባሉ የሚችሉ እና ምናልባትም በቀድሞው የአገሪቱ ፖለቲካ አመራር ውስጥ ያለፉና የእነርሱው ዘመን አካል የሆኑ ምሁራን ደግሞ ግድቡ በግብፃዊያን ህይወት ውስጥ ትልቅ ችግርን የሚያስከትል በመሆኑ በማንኛውም ሁኔታ የግንባታው ሂደት መቋረጥ አለበት የሚል አቋም ሲያራምዱ ይደመጣል፡፡ ይህ ሁለተኛውና የግድቡን ግንባታ በማንኛውም ተጽእኖ ማቋረጥ ይገባል የሚለው አመለካከት አሁንም ድረስ በተወሰነ መልኩ የቀጠለበት ሁኔታ ይታያል፡፡

በህዳሴው ግድብ ዙሪያ በተለይ በግብጽ ዘንድ ያለው አመዛኙ አመለካከት አዎንታዊ ነው ለማለት ያስደፈረኝ ግድቡ ጀምሮ ከአንዳንድ የአገሪቱ ፖለቲከኞች፣ የሚዲያ ተቋማትና ጥቂት ምሁራኖች ሲቀብ ለነበረውና አሁንም ድረስ በወሰነ መልኩ እየቀረበ ላለው ጊዜ ያለፈበትና አፍራሽ አስተሳሰብ ይህ ነው የሚባል ድጋፍ አለመስጠቱ አንዱ ነው፡፡

በተለይ የህዳሴው ግድብ የግንባታ ሂደትን ተከትሎ የወንዙን ተፈጥሯዊ የፍሰት አቅጣጫ የማስቀየሩ ተግባር በተከናወነበት ወቅት የአገሪቱ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና አንዳንድ በወቅቱ የነበረው መንግስት አካል የሆኑ ግለሰቦች

እንጸባርቀውት ለነበረው ፍጹም አፍራሽና ያልሰለጠነ አስተሳሰብ አብዛኛው ግብጻዊያን ምላሽ የአገሪቱን ፖለቲከኞች አቅም ጥያቄ ውስጥ የከተተ እንደነበር ከተለያዩ የግብጽ መገናኛ ብዙሃን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህ ወቅት ኀላፊነት የሚሰማቸው የአገሪቱ መገናኛ ብዙሃንንና ምሁራንን ጨምሮ ከአያሌ ግብጻዊያን ዜጎች የተደመጠው አስተያየት የአገሪቱ ፖለቲከኞችም ሆኑ አገሪቱን ይመራ የነበረው መንግስት በኢትዮያ ላይ በዓለም አደባባይ ይፋ ያደረጉት ጦርነትና ሌሎች አፍራሽ ስልቶች በዚህ ዘመን አገር ይመራል ተብሎ ከሚታሰብ አካል የማይጠበቅ፣ የፖለቲከኞቹን የመምራት አቅም ከፍተኛ ጥያቄ ውስጥ የሚከትና  ግብጽን በዓለም አቀፍ የፖለቲካ መድረክ ላይ ያዋረደ መሆኑን የሚያትት ነበር፡፡

ምንም እንኳ የዚህ ዓይነቱ አፍራሽ አመለካከት ከጊዜ ጊዜ እየቀነሰ የመጣ ቢሆንም አሁንም ጥቂት ግብጻዊያን የፖለቲካ ሰዎች፣ በትምህርታቸው የካበተ እውቀት አላቸው የሚባሉ ግለሰቦችና አንዳንድ የአገሪቱ ሚዲያ ተቋማት ለግብጽም ሆነ ኢትዮጵያው ጨምሮ ለተቀረው የአባይ ተፋሰስ አባል አገራት ህዝቦች ጥቅም የማያመጣ አመለካከት ማስተጋባታቸውን አላቆሙም፡፡ በእነዚህ አካላት ከሚቀርቡት መሰረት የሌላቸው አስተያየቶች መካከል የህዳሴው ግድብ የግብጽን ሁለንተናዊ ደህንነትና ህልውና ለአደጋ ይጥላል በመሆኑም በማንኛውም መልኩ መግታት ያስፈልጋል የሚል ነው፡፡

ሆኖም ግን የኢትዮጵያ መንግስት የህዳሴው ግድብ ለግብጻዊያን ጥቅም እንጂ በምንም መልኩ ጉዳት ሊያመጣ እንደማይችል ገለልተኛ በሆነ ዓለም አቀፍ አጥኚ ቡድን ጭምር እንዲረጋገጥ በማድረግ ከፍተኛ የመግባባትና አብሮ የመስራት ሁኔታ ለመፍጠር በእኔ እይታ ከልክ ያለፈ ጥረቶችን አድርጓል፤ አሁንም በዚህ ተግባሩ ገፍቶበታል፡፡

እነዚህ የአገራችን መንግስት የፖለቲካና ዲፕሎማሲ ጥረቶች የአገራት የጋራ ኃብት የሆኑ ወንዞችን ጨምሮ በሌሎችም ዓለም አቀፍ ህጎችና የችግር አፈታት ስልቶች

ጭምር ፍጹም ተቀባይነት ያለው መሆኑን ሰነዶች ያረጋግጣሉ፡፡ በእኔ እይታ ይህ የኢትዮጵያ መንግስት መንገድ ነው የህዳሴው ግድብን በመለከተ በበርካታ ግብጻዊያንም ሆነ በሌሎች ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ዘንድ አዎንታዊነት ያለውን አቋም ለመፍጠር ያስቻለው፡፡

የሆነው ሆኖ ግን እነዚህ አመለካከቶች ከምን ጊዜውም በላይ በተለይ በአሁኑ ወቅት ባዶ ጩከቶች ከመሆን ውጭ ሌላ ምንም ፋይዳ አይኖራቸውም፡፡ በኢትዮጵያ አባይ ወንዝ ላይ እየተገነባ የሚገኘው የህዳሴው ኃይል ማመንጫ ግድብ ስራ በአሁኑ ወቅት 30 በመቶ ያህሉ መጠናቀቁንና ቀሪው ስራም በመፋጠን ላይ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ የሚመለካቸው የመንግስት ባለስልጣናት እንደሚገልጹት የግድቡ ግንባታ በተያዘለው እቅድ መሰረት በመከናወን ላይ ከመሆኑም በላይ እስካሁን ባለው ሂደትም ምንም ዓይነት የገንዘብ እጥረት አልተከሰተም፡፡ ለግድቡ ግንባታ ያስፈልጋል ተብሎ የሚጠበቀው 80 ቢሊዮን ብር ያህል ነው፡፡

ህዝቡ ለዚሁ ዓላማ ስኬት የበኩሉን ድጋፍ ለማበርከት በገባው ቃል መሰረት መንግስት ከአጠቃላይ የግድቡ ወጪ ውስጥ 20 በመቶውን ከዜጎች ለማሰባሰብ አቅዶ ተንቀሳቅሷል፤ እስካሁን ባከናወነው ተግባርም ይህንን እቅዱን በግማሽ ያህል ማሳካቱን ከመንግስት አካላት የሚወጡ መረጃዎች አረጋግጠዋል፡፡

በእኔ እምነት ከግድቡ ግንባታ ስራ ጋር በተያያዘ ያለው ሂደትና የእስካሁኑ ክንውን በተለይ ግንባታው በምንም መልኩ ሊቆም ይገባዋል ከሚለው ስብከታቸው ላልተገቱት አካላት በርካታ አንደምታዎች ይኖሩታል፡፡

ከሁሉም ቀዳሚ ሆኑ ሊቀርብ የሚችለው አንደምታ መንግስት  በግዙፍነቱም ሆነ በፋይዳው በአፍሪካ ቀዳሚ ደረጃን ይይዛል ተብሎ የሚጠበቀውን ታላቁ የህዳሴ ግድብ ስራን ይፋ ባደረገበት ወቅት ግድብ አገር ውስጥ ከሚገኝ ኃብት ለመገንባት በመንግስት የተገለጸው ቁርጠኝነትና በህዝቡ ዘንድም የተንፀባረቀው አገራዊ መነሳሳት ውጤታማነት ተጨባጭ የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡

ይህ የግድቡ ግንባታ ሂደት ያለምንም ሳንካ በተሳካ ሁኔታ መቀጠሉና አሁን ላለበት ደረጃ መድረሱ የአገሪቱ መንግስትና ህዝብ ለህዳሴው ግድብ እውን መሆን ያላቸው ቁርጠኝነት ሊቀለበስ የማይችል፣ የግድቡ ግንባታም በተባበረ የአገር ውስጥ አቅም ተገንብቶ ለፍሬ የሚበቃ እንጂ የሚቋረጥ አሊያም የሚዘገይ አይሆንም ሲሉ የተለያዩ የውጭ አገራት ታዛቢዎች ጭምር እየተመሰከሩ ናቸው፡፡

ለእኔ ግድቡ ለአሁን ላለበት ደረጃ የበቃበት ሁኔታ ሌላም ትርጉም አለው፡፡ አንዳንዶች አውቀውም ይሁን ሳያውቁ የግድቡን ዓላማ በአፍራሽ መልኩ በማየት ሌሎች ደግሞ አገሪቱንና ህዝቧቿን በወጉ ካለመረዳት ሊሆን በሚችል ምክንያት ግድቡ ሊሳካ የማይችል፣ የማይጨበጥና በወረቀት ላይ የሚቀር ህልም በማለት የሰጡትን ጨለምተኛ አመለካከት አሸንፏል የሚል እምነትም አሳድሮብኛል፡፡

ከሁሉም በላይ ግን ግድቡ በመላው ኢትዮጵያዊያን ልብ ውስጥ ትልቅ ስፍራ የተቸረው ከመሆኑም በላይ መላው ህዝብ የማንነቱ መገለጫ፣ ሰንደቅ ዓላማውና ታሪኩ እንዲሆን የሚሻ መሆኑንም በጉልህ ያሳያል፡፡

ከዚህ የአገሬ ህዝብ እውነት ጋር በተያያዘ የአንድ ግብጻዊ ምሁርን አስተያየት ልጥቀስ፡፡ በግብጽ ፖለቲካ ውስጥ ሁነኛ ስፍራ እንዳላቸው የሚነገርላቸው መምዱህ ሃምዛ የናስር ግድብ ለግብጻውያን እንደሚጠቅምና ግብጻውያን እንደሚያከብሩት ሁሉ ኢትዮጵያዊያንም ታላቁ የህዳሴ ግድብ እውን እንዲሆን ያላቸው ህልም ያንኑ ያህል ሃያል ነው፣ ኢትዮጵያውያን በአሁኑ ወቅት የህዳሴውን ግድብ እንደ አንድ ብሔራዊ የደህንነታቸውና የጥቅማቸው ጉዳይ አድርገው ነው የሚመለከቱት የሚል አስተያየት ለአንድ የአገሪቱ ሚዲያ ሰጥተዋል፡፡

ጀአን ዮ የተባሉ ተንታኝ ደግሞ Super Dam: Egyptian Concern for Nile Water Security Spurs Cooperation over Ethiopia's New Dam በሚል ርዕስ ከወር በፊት ባቀረቡት ጽሁፍ ኢትዮጵያዊያን የህዳሴው ግድብን በታላቁ የአሜሪካን የኢኮኖሚ ቀውስ ወቅት እንደተገነባው የሁቨር ግድብ የኢኮኖሚ እና ፖለቲካዊ ልማት ስኬት አድርገው ይቆጥሩታል የሚል አስተያየት ሰንዝረዋል፡፡

በኢትዮጵያው የቀድሞው አሜሪካ አምባሳደር የነበሩት የፖለቲካ ተንታኝ አምባሳደር ዴቪድ ሺን ኢትዮጵያ በራሷ አቅም እየገነባችው ያለው የኃይል ማመንጫ ግድብ ላለፉት ዘመናት በላይኛው የወንዙ ተፋሰስ ለሚከናወኑ ማናቸውም ፕሮጀክቶች ከታታላቅ አበዳሪዎች ብድር እንዳይገኝ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ስትጫወት ለነበረችው ግብጽ "ጨዋታውን የቀየረ" ነው ሲሉ ጠቅሰው በአሁኑ ወቅት የህዳሴው ግድብ ግንባታ ስራ የደረሰበት ደረጃና የስራው ፍጥነት ግድቡ ሊቋረጥ የሚችልበት መሰረት የሌለ መሆኑን ያሳያል ብለዋል፡፡

አምባሳደር ሺን አያይዘውም ግብጽ የውኃ ፍላጎቷን ማስከበር የምትችለው የምሥራቅ አፍሪካ ኢኮኖሚን ወደ ኢንዱስትሪ በማሸጋገር ረገድ "ትልቅ ለውጥ ሊያመጣ" ከሚችለው ከህዳሴው ግድብ ፕሮጀክት ጋር ስትተባበር ብቻ ነው የሚል ሀሳብም አቅርበዋል፡፡

አምባሳደር ሺን እንደሚሉት ኢትዮጵያ በቀጣናው የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እንዲጨምር በማድረግ ረገድ ግዙፍ አስተዋጽኦ ለማድረግ አቅም አላት፤ ይህም ኢትዮጵያ ያለባትን ሁሉንም  የኃይል ፍላጎቶች ለማሟላት፣ ለጎረቤት አገራት በትርፍ ኃይል ለመሸጥ፣ በጎረቤት ሱዳን በተደጋጋሚ የሚከሰተውን ጎርፍ ለመከላከል እና ለቀጣናው ኢኮኖሚያዊ ውህደት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማድረግ ያስችላል።

የአፍሪካ ህብረት ዓለም አቀፍ ጉዳዮች አማካሪ በኔቶ መከላከያ ኮሌጅ ተመራማሪ ዶክተር መሃሪ ታደለ ማሩ በመንግሥታት ፖለቲካዊ ዕይታ ካልተበረዘ በስተቀር ናይል እና ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ጨምሮ ሌሎች በተፋሰሱ አገራት ውስጥ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች የየትኛውንም አገር ወይም ህዝብ ደህንነት ስጋት ውስጥ አይከቱም የሚል እምነት እንዳላቸው መግለጻቸውን አንብቤያለሁ፡፡

በአገራቱ መካከል ትብብር ከተፈጠረ የግድቡ ግንባታ ናይል በታሪክ የጥላቻ ምንጭነት ከመሆን ይልቅ በተፋሰሱ አራት ሕዝቦች መካከል የለውጥ ድልድይ ሊሆን እንደሚችልም ዶክተር መሃሪ ምሁራዊ አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል፡፡

ዶክተር መሃሪ አክለውም ግብጽ የናይል ውኃን በብቸኝነት ይዞ ለመጓዝ የመፈለግ አቋሟን በመለወጥ ከተፋሰሱ አገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ገንቢ በሆነ መልኩ ለማስተካከል መንቀሳቀስ ይኖርባታል የሚሉት ዶክተር መሃሮ በተመድ፣ በአፍሪካ ልማት ባንክ፣ በዓለም ባንክ፣ ካናዳ፣ በአውሮፓ ኅብረት እና ጃፓን በኩል የናይል ተፋሰስ ኢንሺየቲቭ በዓለማቀፍ ሕግ መሠረት እና በዓለማቀፉ ማኅበረሰብ ድጋፍ የትብብር አጋርነት ስልት ድጋፍ ስላለ ግብጽ የትብብር ስምምነት ማፅቀፉን መፈረም እና በናይል ተፋሰስ ኢንሺየቲቭ መሠረታዊ መርሆዎች ጥላ ስር ልዩነቷን መፍታት አለባት በማለት አብራርተዋል።

ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ተንታኞች እንዲያውም የግብጽና ሱዳን መንግስታት የወንዙን ተጠቃሚነታቸውን በአግባቡ ማረጋገጥ የሚችሉት ስምምነቱንና በወንዙ ላይ የሚካሄዱትን የልማት ፕሮጀክቶች በመቃወም ሳይሆን ስምምነቱን በመቀላቀል ከሌሎቹ የተፋሰሱ አባል አገራት ጋር በጋራና በመነጋገር ለመስራት ከተስማሙ ብቻ መሆኑንም ይመክራሉ፡፡

ይህ የምሁራን ተጨባጭ ትንተና የግድቡን ግንባታ ለማሳካት መንግስትና ህዝብ ያሳዩት ርብርብና የተገኘው ውጤት ያመጣው እውነት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ከዚህም ሌላ ይህ እውነት አብዛኛውን የግብጽ ፖለቲከኛ አመለካከት በአዎንታዊ መልኩ ገርቶታል የሚል ግምት አለኝ፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያቴ እላይ የጠቀስኳቸው ጥቂት ጦርነት ናፋቂዎች ህልም እንዳለ ሆኖ ካለፉት ሁለት ወራት ጀምሮ ከአገሪቱ የፖለቲካ መሪዎች አካባቢ የሚወጡት ለየት ያሉ አስተያየቶች ናቸው፡፡

በግብጽ የመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት የተስጋቡት እነዚህ አስተያየቶች የሚያንጸባርቁት ኢትዮጵያ ውስጥ በአባይ ወንዝ ላይ የሚገነባውን ታላቁ የህዳሴ

ኃይል ማመንጫ ግድብ ለማስተጓጎል ከማሰብ ይልቅ ከአገሪቱ ጋር አብሮ መስራት በሚቻልበት መንገድ ላይ ማተኮር ይገባል የሚል አመለካከትን ነው፡፡

የግብጹ የውሃና መስኖ ሚኒስትር መሐመድ አብዱል ሙጠሊብ አል - ሞኒተር ከተሰኘ ጋዜጣ ጋር ባካሄዱት ቃለ ምልልስ የኢትዮጵያ መንግስት በማስገንባት ላይ ያለው የህዳሴ ግድብ ለኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅምና ልማት እስከዋለና ግብጽን ለጉዳት የማይዳርግ እስከሆነ ድረስ የግብጽ መንግስት ቢደግፈው ምንም አይነት ቅሬታ ሊኖር አይገባም የሚል አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

ሚኒስትሩ በዚሁ ቃለ ምልልሳቸው ግደቡ ስለሚይዘው የውሃ መጠን፣ ለመሙላት የሚፈልገው ጊዜና ስለሚኖረው የውሃ ፍሰት በተመለከተ መግባባት ላይ ከተደረሰ በግድቡ ግንባታ ላይ ለመሳተፍ ፈቃደኞች ነን የሚል ገንቢ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ ይህም የመንግስታቸው አቋም መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በዚሁ ጋዜጣ ላይ የተጠቀሱ ሌላ የግብጽ ከፍተኛ ባለስለጣን የግብጽ መንግስት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በህዳሴው ግድብ ግንባታ ዙሪያ ለመደራደር ሰነድ እያዘጋጀ መሆኑን ይፋ አድርገዋል፡፡ ምንም እንኳ ጋዜጣው በስም ያልጠቀሳቸው እኚህ የግብጽ መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣን የጠቀሱት ሰነድ በእኔ እምነት በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ተቀባይነት ላያገኙ የሚችሉ ጥቂት የግብጽ ፍላጎቶች የሚንጸባረቁበት ቢሆንም
ሰነዱ የሚይዛቸው የመደራደሪያ ነጥቦች የሚሽከረከሩት ግንባታው እንዲቆም አሊያም እንዲዘገይ በሚያደርጉ ሀሳቦች ሳይሆን ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር በትብብር የመስራት ሁኔታን ማምጣት በሚቻልበት ሀሳብ ላይ ነው፡፡

ከዚሁ የአቋም ለውጥ ጋር በተያያዘ ሌላው ሀሳብ ያቀረቡት ሰይፉልአዚዝ ሚላስ የተባሉ ግብጻዊ የፖለቲካ ተንታኝ ናቸው፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት የሕዳሴው ግድብ እና የሚያመነጨው 6ሺህ ሜጋ ዋት ኃይል ለሁሉም የናይል ተፋሰስ አገራት ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው ብሎም በቀጣናው ኢኮኖሚያዊ ውህደት፣ ሰላም እና ደህንነት እንዲፈጠር የሚያስችል በመሆኑ ተቀራርቦ መስራት ይበጃል፡፡

የግብጽ የቀድሞው የመስኖ ሚኒስትር ዶ/ር መሀመድ ነስአልዲን አላም የኢትዮጵያ መንግስት ከግብጽ አቻው ጋር በህዳሴው ግድብም ሆነ በሌሎች የጋራ ጥቅሞች ላይ ተቀራርቦ ለመስራት የሚያሳየውን ዝግጁነት አድንቀዋል፡፡ ከኢትዮጵያ መንግስት የሚወጡት መግለጫዎች ገንቢና ግብጻውያን የህዳሴው ግድብ ሊያሳስባቸው እንደማይገባና ኢትዮጵያ በግብጽ ላይ ጉዳት ታደርሳለች ብለው እንዳይጠራጠሩ የሚያደርግ ነው ሲሉ ለዘገራቱ ሚዲያዎች መግለጻቸውም ሊነሳ የሚገባው የግብጽ አቋም ማሳያ ነው፡፡

ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው የፖለቲካ ተንኞች የሚመክሩትም ይህንኑ ነው፡፡ ይህም ግብፅ ከአባይ ወንዝ አጠቃቀም ጋር አለኝ የምትለውን ስጋት ማስወገድና የውሃውን ተጠቃሚነቷን ማረጋገጥ ትችል ዘንድ ከሁሉም የአፍሪካና በተለይ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ግንኙነት ማጠናከር የግድ ይላታል፡፡

ከዚህም ሌላ ግብጽ ከወንዙ ጋር በተያያዘ አለኝ የምትለውን መብት ለማስከበር የቀድሞዎቹ ስርዓቶች ሲያደርጉት እንደነበረው ዓይነት ባዶ ዛቻና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድጋፍ ማስተጓጎልን የመሳሰለ ተጽእኖ የመፍጠር መንገድ ለማራመድ የሚያስችላት ዘመን ማለፉንና ተጨባጩ የዓለም ሁኔታ መንገዱን እንደቀየረውም ያሳያል፡፡ ግድቡና የእስካሁኑ የኢትዮጵያ መንግስት የትብብር ዲፕሎማሲ ሂደት የሚያረጋግጠው ሌላው ትልቅ ቁም ነገርም ግድቡ ሊገታ የማይችልበት ደረጃን የተጎናጸፈ በመሆኑ በኃይል የሚመካውን አስተሳሰብ በትብብር ዲፕሎማሲ እንዲተካ ማድረጉን ጭምር ነው፡፡ የእስካሁኑ ውጤታማ ክንውን የቀድሞውን በተጽእኖ የተሞላ አፍራሽ ጨዋታ ቀይሮታል፡፡

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ከጥቂት ግብጻዊያን ዘንድ የሚስተጋባው የህዳሴውን ግድብ የማስቆም ህልም በምንም መለኪያ የትም ሊደርስ የማይችል መሆኑን የአስተሳሰቡ አራማጆች ሊቀበሉት ይገባል፡፡ እነዚህ አካላት ከዚህ ይልቅ አገራቸውንና ህዝባቸውን ሊጠቅም የሚችለው ተቀራርቦ በጋራ መስራት መሆኑን

ማጤን ይኖርባቸዋል፡፡ በጋራ የወንዞች አጠቃቀም ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶችም ሆኑ የተለያዩ ስራ ላይ የዋሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችም አበክረው የሚመክሩት ይህንኑ ነው፡፡